## ማሳሰቢያ

የተወደዳችሁ የአሰረ ሐዋርያት ተማሪዎች

ይህ ላለፉት ሳምንታት ከተነጋገርንባቸው ዋና ዋናዎቹን ሀሳቦች በአስተዋጽኦ መልክ ለ ማቅረብ የተሞከረበት ጽሁፍ ነው። ጽሁፉ መሰረታዊ የሆነውን የጥናታችንን ፍልስፍና ስለሚያስጨብጥ ጠቃሚ ስለሆነ ብትመለከቱት መልካም ነው።

የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናት እንደሌሎቹ ጥናቶች ሁሉ ጊዜ መሰጠትን የሚጠይቅ ነው። ስለ ሆነም በክፍል ውስጥ የተወያየንባቸውን ነገሮች በቤታችን ውስጥ ጊዜ ሰጥተን ካየነው የ ጥናቱን ውጤት እናገኘበታለን። በሌላ በኩል ደግሞ የመጽሀፍ ቅዱስ ባለቤት እግዚአብ ሄር መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ እውነተኛ የሆነውን የቃሉን ምስጢር እንዲገልጥልን ወደ አ ምላካችን በጸሎት ልንቀርብ ይገባናል።

«ደግሞም የወንጌልን ምስጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘን ድ ስለእኔ ለምኑ» በማለት ሀዋርያው ተከታዮቹን በጸሎት እንዲያስቡት ለምኖአለቸው ነበር። ኤፌ 6፥19። ይህም የቱንም ያህል ብናጠና የቱንም ያህል ብናነብ እውነተኛ መገለጥ የሚመጣው የቃሉ ባለቤት ከሆነው ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የእግዚአብሄር ቃል እነዚህን ሶስት ዋና ዋና ነገሮች ይፈልጋል።
1ኛ. በእምነት መቅረብ፤ የእግዚአብሄርን ቃል አምነን መቅረብ፤ በጥርጥርና በሰዋዊ ሀሳ ብ አለማንበብ።

2ኛ. በመታዘዝ መቅረብ፤ የእግዚአብሄርን ቃል የምናነበው አማራጭ ሀሳብ ለማግኘት ሳ ይሆን በፍጹም መታዘዝ የእግዚአብሄር ቃል ነው ብለን ልንከተለው ነው። ስለሆነም ቃ ሉን አሜን ብለን ልንታዘዝ ይገባል።

3ኛ. ከህይወታችን ማዛመድ፤ «ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው» የሚለው የጌታችን ንግግር ቃሉን መስማት አሜን ማለት ብቻ ሳይሆን በህይወታችንም ልንተረጉመው ይገባናል፤ ል ናስተውለው የሚገባን አለምን ልንለውጥ የምንችለው ትልቅ ጭንቅላት (አዋቂነት) ይዘ ን ሳይሆን፥ በጸሎት የደከሙ ጉልበቶችን በፍቅር የተሞሉ ልቦችን በጸጋ የተቀመሙ አ ንደበቶችን ይዘን ነው።

አብረን በወንጌል እርሻ ውስጥ የምንደክም ስለሆንን በትምህርታችን ውስጥ ጥያቄ፣ ሀሳ ብና አስተያየት ቢኖራችሁ ከመጠየቅ ወደ ሁዋላ እንዳትሉ። በተቻለ መጠን ትምህርቱ ን ያለማቋዋረጥ ለመከታተል ሞክሩ፤ በችግር ምክንያት ባትመጡና ብትደውሉልኝ ደግ ሞ ትምህርቱን በሌላ መንገድ ለመሸፈን እንሞክራለን

የእግዚአብሄር ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሁን።
ቀሲስ መልአኩ ባወቀ ተረፈ
አዲሱ የቤት ስልክ 310 558 8763

## ኦርቶዶክሳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ።

### ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ለምን አስፈለገ?

### 1. የሃይማኖታችን መሠረት ስለሆነ ነው።

እምነታችን በሙሉ የተመሠረተው በመጽሀፍ ቅዱስ በተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ላይ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጻችሁ ዋል» ብሎ ሲናገር የነቢያትና የሐዋርያት ትምህርት በበብሉይና በአዲስ ኪዳን የተገለ ጠው እንደሆነ ለማንም ግልጥ ነው።

### 2. በሃይማኖት ለማደግ ነው።

ክርስቶስ በደሙ መፍሰስ የሰጠን አዲስ ህይወት «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር » ነው (1ጴጥ 2፥24)። ለጽድቅ መኖር የሚለው ቃል ቅድስናንን ወይም በጥቅል አጠራ ሩ ክርስቲያናዊ ኑሮን ያሳያል። በክርስትና ለማደግ የግድ የምእመናን ምግበ ነፍስ የሆነ ው የእግዚአብሄር ቃል ያስፈልገናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «ለመዳን በእርሱ እን ድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ህጻናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ» እንዳለ ው (2፥2-3)፥ በክርስትና ህይወታችን ለማደግ የእግዚአብሔር ቃል የግድ ያስፈልገናል።

### 3. ከዲያብሎስ ፈተና ለመጠበቅ

ቅዱስ ጳውሎስ «ውጊያችን ከሥጋና ከደም (ከሰው) ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከስል ጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ አለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈ ሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» በማለት ክርስቲያን ነኝ ብሎ የሚያምን ሁሉ ከዲያ ብሎስ ጋር የሚጠብቀውን ሰልፍ ግልጥ አድርጎልናል። (ኤፌ 6፥12)። ይህን ውጊያ የም ናሸንፈው ለውጊያው የሚያስፈልገውን የጦር መሣሪያ ስንይዝ ነው። ይህን አስመልክቶ ሀዋርያው ሲያስተምረን «ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆ ም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ አንሡ..... እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው» ይለናል (ኤፌ 6፥13-17)። ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስን ድል ያደረገው ከእግዚአብሔር ቃል እየጠቀሰ ነበር። ማቴ 4፥1-11።

### 4. ራስን ከፈተና ለመጠበቅና ለንስሐ ህይወት ለመዘጋጀት

ቅዱስ ዳዊት «ህግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው» በማለት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ስንራመድ የህይወታችን አቅጣጫ የጠራና የተስተካከለ እንደሚሆን አስ ተምሮናል። አብዛኛዎቹ ፈተናዎቻችን የሚመነጩት ከራሳችን ውስጣዊ ምኞት ነው። ይ ህንንም የሀጢአት ምኞት ለመፈጸም ራሳችንን በብዙ እናታልለዋለን። ያን ጥልቅ የሆነ ውን የሰው እውነተኛ ሀሳብ የሚገልጠው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ለዚህም ነው ቅዱ ስ ጳውሎስ «የእግዚአብሄር ቃል ህያው ነውና የሚሰራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንም ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል። በእርሱ አይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተ ራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም» ያለው። በእግዚ

አብሔር ቃል ፊት የሰው ሀሳብ አመክንዮአዊ ንግግር የሰውን ጠሊቅ የሆነ ምሥጢር ሊደብቅ አይችልም። በእርግጥም በእርሱ ፊት የተሰወረ የለም።

5. ከአባቶቻችን የተቀበልነው ሐላፊነትም ስለሆነ ነው።

ለመጽሐፍ ቅዱስ ምስክር ከሆኑት በጣት የሚቆጠሩ ቋንቋዎች አንዱ ግእዝ ነው። የግ እዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ዛሬ አንድን የመጽሀፍ ቅዱስ ትክክለኛ ንባብ ለማወቅ የሚደረገው ምርምር ላይ ምስክር የሆነ ነው። በአለም ካሉት ቻንቻዎች ውስጥ ለዚህ የበቁት ከዋናዎቹ ከግሪክና ከእብራይስጥ ሌላ ሱርስት (ሲሪያክ) ቅብጥ (ኮብት) ሮማይስ ጥ (ላቲን) ብቻ ናቸው። ይህን የግእዝ ትርጉም ለአለም ያበረከተች ቤተ ክርስቲያን ል ጆች ሆነን የመጽሀፍ ቅዱስ እውቀታችን ውሱን ከሆነ የታሪክ ፍርደኞች ነን።

## ኦርቶዶክሳዊ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናት ምን ዓይነት ነው?

1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። (Biblical)

ይህ ማለት ኦርቶዶክሳዊ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናት በራሱ በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረ ተ ነው። መጽሀፍ ቅዱስን በሚገባ የሚተረጉመው ራሱ መጽሀፍ ቅዱስ ነው። ስለሆነም ጥናታችን ለራሱ ለመጽሀፍ ቅዱስ ክብር የሰጠ መሆን አለበት። መጽሀፍ ቅዱሳዊ ነው ስንል በሌላ በኩል መጽሀፍ ቅዱሳዊ በሆነ ሀሳብ የሚጠና ማለታችንም ነው። ሳይንሳዊ ወይም ፍልስፍናዊ ካልን በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ ሰዋዊ ሀሳብን ከፍ አደረግን ማለት ነ ው። በምእራቡ አለም ያለው ችግር ከዚህ መሰረታዊ ስህተት የመጣ ነው።

2. ትውፊታዊ ነው። (Traditional)

ትውፊት ማለት «በቅብብሎሽ የመጣ» ማለት ነው። የያዝነው መጽሀፍ ቅዱስ እኛ እ ጅ የደረሰው ድንገት ከሰማይ ዱብ ብሎ አይደለም። እንደዛሬው ማተሚያ ሳይኖር ብራ ናውን አዘጋጅተው በብእር ጽፈው እዚህ ያደረሱልን አባቶቻችን ናቸው። አባቶቻችን መጽሀፍ ቅዱስን ጠብቀው ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደምናነብና እንደምናጠ ና አስተላልፈውልናል። አንድን የመጽሀፍ ቅዱስ ንባብ ትርጉም ብንፈልግ መጀመሪያ የ ቀደሙት አባቶች እንዴት አድርገው ነው የተረጎሙት ብለን ልንመረምር ይገባናል።

3. ቤተ ክርስቲያናዊ ነው።(Ecclesiological)

በኦርቶዶክሳዊ ነገረ መለኮት መሰረት መጽሀፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ያፈራችው ነው። ማለት ጸሀፊዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሰረት የሆኑት ሀዋርያትና ነቢያት ናቸው። ከዚህም ሌላ የትኞቹ መጻህፍት አምላካውያት መጻህፍት እንደሆኑ በቀኖና (ካኖን) የለየችው ቤተ ክርስቲያን ነች። እነዚህን መጻህፍት ስትሰጥ ፍጹም የሆነው የመጽሀፍ ቅዱስ ትር ጉም በራሱ በመጽሀፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን በጸጋ በሚጠቀምባት በቤተ ክርስቲያን፣ በአን ድነትና በፍቅር በምታዘጋጃቸው ጉባኤዎቹዋ ውስጥ እንደሚገኝ እናምናለን። በዚህም ምክንያት አንድ ኦርቶዶክሳዊ አንድን የመጽሀፍ ቅዱስን ክፍል ሲመረምርና ሲያጠና የ ሚያጠናው ብቻውን ሳይሆን ከማህበረ ምእመናኑ ጋር ነው። በዚህም ምክንያት በትርዋ ሜው ውጤት ላይ የቤተ ክርስቲያን አካልነቱ ውጤት ይገለጣል እንጂ «ለእኔ የተገለጠ

ው ይህ ነው፤ የኔ መገለጥ እንዲህ ነው» የሚል አይሆንም። ይህ ማለት በጥናቱ ሂደት ውስጥ በማህበረ ምእመናኑ የቤተ ክርስቲያን አበው ሚና ጎልቶ ይታያል።

4. ክርስቶሳዊ ነው። (Christological)

ኦርቶዶክሳዊ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናት ክርስቶስን ማእከል ያደረገ ነው። ክርስቶስን ማእ ከል ያላደረገ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናት፣ የመጽሀፍ ቅዱስን መሰረታዊ ሀሳብ የሳተ ነው። መጽሀፍ ቅዱስ የሰው ልጅ የደህንነት ታሪክ ነው። በሌላ አነጋገር ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ራዕየ ዮሐንስ ድረስ የምንመለከተው በሴቲቱ ዘርና በእባቡ መካከል የተደረገውን ጦርነትና የሴቲቱ ዘር እርሱም ክርስቶስ እባቡን እንዴት ድል እንዳደረገው ነው። ዮሀ ንስ ራእይ የሚፈጸመው በዘንዶው ወደ የዘላለም እሳት መጣል ነው። መጽሀፍ ቅዱስ ይህን ሊያሳየን በጥንቃቄ የክርስቶስን ታሪክ ይከተላል። ከቃየን ይልቅ የሴትን ትውልድ፣ ከሁለቱ ወንድሞቹ ይልቅ የሴምን፣ ከሌሎቹ ይልቅ የአብርሃምን፣ ከእስማኤል ይስሐ ቅን፣ ከኤሳው የያእቆብን፣ ከአስራ ሁለቱ ውስጥም የሌዊንና የይሁዳን፣ ከይሁዳም ዘር የዳዊትን ሀረገ ትውልድ ሲከተል እናያለን። ይህም አለምክንያት ሳይሆን የመሲሁን አ መጣጥ ለማሳየት ነው። ለእኛ ለክርስቲያኖች ክርስቶስ የደህንነታችን ራስና መሰረት ነ ው። ስለሆነም በእያንዳንዱ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናታችን ላይ የክርስቶስን ሰው የመሆን ምስጢርና የማዳን ስራ ልናተኩርበት ይገባል።

5. አምልኮአዊ ነው።። (Liturgical)

ኦርቶዶክሳዊ ቤተ ክርስቲያን መጽሀፍ ቅዱስን የምትተረጉመው ደረቅ ከሆነ የምርምር አቅጣጫ ሳይሆን ከአምልኮ መንፈስ ነው። ኦርቶዶክሳዊ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናት አምል ኮአዊ ነው ስንል በጸሎታችን በቅዳሴያችን በስብከታችን የምንተረጉመው ነው። ይህ የ ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ህይወት ነው ቀድሞም መጽሀፍ ቅዱስን ያስገኘው። አሁንም ቤተ ክርስቲያን የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናትዋ መመለክና መመስገን ወደሚገባው ወደ ልኡ ል እግዚአብሔር መቅረቢያ መንገድ ነው። በዚህም ምክንያት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክር ስቲያን በአምልኮ ጊዜያቱዋ በቅዳሴዋ መጽሀፍ ቅዱስ ማእከላዊ ስፍራ እንዲኖረው ታ ደርጋለች።

6. ምስጢራዊ ነው።(Sacramental)

ይህ ከላይ ካየነው ጋር የሚገናኝ ነው። ምስጢራዊ ስንልም ድብቅ ማለታችን ሳይሆን ጸ ጋ እግዚአብሄርን የምናገኝበት ነው። እውነተኛ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናት ወደ ንስሀና ወ ደ ቅዱስ ቁርባን የሚያቀርበን መሆን አለበት፣ በትዳር ህይወታችን ፍቅርን ሰላምን (ም ስጢረ ተክሊል) በህመማችን ፈውስን (ምስጢረ ቀንዲል) የሚሰጠን ነው።

8. ሰማያዊ ነው።(Eschatological )

በቅዳሴ ጊዜ ድምጻችንን ከፍ አድርገን «የሚመጣውን ህይወት ተስፋ እናደርጋለን» ብ ለን ሃይማኖታችንን እንገልጣለን። በዚህም እምነታችን ዘላለማዊ ህይወትን ተስፋ በማ ድረግ ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ እናስረግጣለን። እውነተኛ ኦርቶዶክሳዊ የመጽሀፍ ቅዱ ስ ጥናት ምእመንን ለሰማያዊ ህይወት የሚያዘጋጅ ነው። ይህ ማለት በዚህ ምድር ያለ ንን ሀላፊነት የሚያስረሳን ሳይሆን ህይወታችንን ሁሉ ከሰማያዊው ኑሮአችን አንጻር እን ድንመለከተው የሚያደርገን ነው። «እኛ አገራችን በሰማይ ነውና። ከዚያም መድሀኒትን

እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤» (ፊል 3፥20) ብሎ ሐዋርያው እንዳስተማረን የሰማዩን ርስታችንን ለመቀበል በዚህ ምድር በዘላለማዊ ተስፋ እንዴት መራመድ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ይህ በአሁኑ ወቅት መጽሐፍ ቅዱስን የእለት ችግራችንን መፍቻ (ሰልፍ ሄልፕ) መጽሐፍ አድርጎ ከመመልከት አደጋ የሚያድነን ነው። ሀዋርያው ከዚህ አደጋ እንድንጠበቅ ሲያስጠነቅቀን «በዚህች ህይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን»።

9. አውዳዊ ነው።(Contextual)

ኦርቶዶክሳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ መጽሐፍ ቅዱስን ማለትም ብሉይ ኪዳንን ለሙሴና ለነቢያት አዲስ ኪዳንንም ለሐዋርያት የሰጠው ያው አንዱ እግዚአብሔር እንደሆነ ትኩረት ያደርግበታል። በዚህም ከመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመናት ጀምሮ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ብሉይ ኪዳንን ፍጹም አምላካዊ እንዳይደለ ወይም አንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተቀባይነት እንደሌለው አድርገው ይናገሩ የነበሩትን ከጉባኤዋ ለይታቸዋለች። ለምሳሌ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ማርሲዮን (መርቅያን) የተባለው ብሉይ ኪዳንን የሰጠው ክፉ አምላክ ነው አዲስ ኪዳንን የሰጠው ደግ አምላክ ነው ብሎ ብሉይ ኪዳንን ለማቃለል ሲሞክር ቤተ ክርስቲያን አወገዘችው እንጂ አልተቀበለችውም። ጌታም የብሉይ ኪዳን መጻህፍት በእስትንፋሰ እግዚአብሔር የተጻፉ በመሆናቸው በእግዚአብሄር ጥበቃ ውስጥ መሆናቸውን ሲያስረግጥልን «እውነት እላችሃለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከህግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም።» ብሎናል( ማቴ 5፥18)

ይህን ያተትነው አለምክንያት አይደለም። ኦርቶዶክሳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በአንድ ግንጥል ጥቅስ ላይ በመመርኮዝ መጽሐፍ ቅዱስን አይተረጉምም፥ ዶግማንም ሆነ ቀኖናን አይመሠርትም። ጥቅሱን ከምዕራፉ፥ ምዕራፉን ከመጽሀፉ፥ መጽሐፉን ከሌሎች መጻህፍት፥ ብሉይን ከአዲሱ፥ አዲሱን ከብሉዩ ማስተያየት ኦርቶዶክሳዊ የአተረጉዋጎም መንገድ ነው።

10. አምሳላዊ ነው። (Symbolical)

ከመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የጥንቱዋን ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መንገድ ስንመለከት ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን የምታጠናው በጥሬ ንባቡ ብቻ አልነበረም። ይህንንም የአተረጉዋጎም መንገድ ያገኘችው በተለይ ከቅዱስ ጳውሎስ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ የእስራኤልን የምድረ በዳ ጉዞ በተረጎመበት ንባቡ ላይ ስለ ክርስቶስ እንዲህ ነበር ያለው «ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ። ሁሉም በባህር መካከል ተሻገሩ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባህር ተጠመቁ። ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ። ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ። ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ድንጋይ ጠጥተዋልና፥ ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበረ።» 1ቆሮ 10፥1-4።

ቅዱስ ጳውሎስ የእስራኤላውያንን የምድረ በዳ ጉዞ ሲያነብ ይታየው የነበረው ክርስቶስ ነበረ። በዚህም ምክንያት በምድረ በዳ ለጥማቸው ርካታ የነበረው ያ አለት ክርስቶስ ነው ብሎ ተረጎመው። ይህ ከጥሬ ንባቡ የዘለለ አተረጓጎም ነው። ያ አለት በጊዜና በቦ

ታ የተወሰነ ታሪካዊ ክስተት የተከናወነበት ቢሆንም ሊመጣ ላለው ለክርስቶስ ምሳሌና ጥላ እንደሆነ ሀዋርያው ያሳየናል።

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ብቻ አይደለም ይህን አተረጓጎም የተጠቀመው። ስለ ህግ ና ወንጌል ለገላትያ ክርስቲያኖች ሲያስተምራቸው አጋርንና ሳራን ከሲና ወይም ከኢየሩ ሳሌምና ከሰማያዊት ኢየሩሳሌም ጋር እንዴት እንዳነጻጸራቸው እንመልከት። «አንዱ ከባሪያይቱ አንዱም ከጨዋይቱ የሆኑ ሁለት ልጆች ለአብርሃም እንደነበሩት ተጽፎአል ና። ነገር ግን የባሪያይቱ ልጅ እንደ ሥጋ ተወልዶአል። የጨዋይቱ ግን በተስፋ ቃል ተ ወልዶአል። <u>ይህም ነገር ምሳሌ ነው።</u> እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለቱ ኪዳኖች ናቸውና። ከደብረ ሲና የሆነችው አንዲቱ ለባርነት ልጆችን ትወልዳለች። እርሱዋም አጋር ናት። ይህችም አጋር በአረብ ምድር ያለችው ደብረ ሲና ናት። አሁንም ያለችውን ኢየሩሳሌ ም ትመስላለች። ከልጆቹዋ ጋር በባርነት ናትና። ላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ግን በነጻነት የ ምትኖር ናት። እርስዋም እናታችን ናት።» ገላ 4፥22-26።ይህን የጳውሎስን አተረጓጎም ስናነብ ቤተ ክርስቲያናችን ከምትጠቀምበት የአንድምታ መንገድ ጋር ምን ያህል ተመሳ ሳይነት እንዳለው እናያለን።

ይህ አተረጓጎማችን ክርስቶስን መሰረት ያደረገ ስለሆነ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ውስጥ መሰረታዊ የሆነውን ሀሳብ እንድናስተውል ይረዳናል። ቅዱስ አውግስጢኖስ የተ ናገረው ላይ ተመስርተን

ብሉይ ኪዳን ጥላ ነው፤ አዲስ ኪዳን አካል ነው።
ብሉይ ኪዳን ትንቢት ነው፤ አዲስ ኪዳን ፍጻሜ ነው።
ብሉይ ኪዳን ንባብ ነው፤ አዲስ ኪዳን ትርጓሜ ነው።
አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተደብቆአል።
ብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተገልጦአል።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ይህን አተረጓጎም በመጠቀም ነው የክርስቶስን የባህርይ አም ላክነት የቤዛነትና የአዳኝነት ስራ የምትተረጉመው። የክርስቶስን ሰው የመሆን ምስጢር አምልታ አስፍታ ስትናገርም ማህጸኑዋን አለም አድርጎ ይህን ድንቅ ምስጢር ስለአከና ወነባት እናቱም ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ከብሉይም ሆነ ከአዲስ ኪዳን ምንባባት ላይ አባቶች የሚተረጉሙት ይህንን መሰረት አድርገው ነው። በዚህ ጥናታችን ውስጥም ይህን አተረጓጎም በሰፊው ለመጠቀም እንሞክራለን።